# በጉለሌ ክፍለ ከተማ ት/ፅ/ቤት የ2016 ዓ.ም የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የስድስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ሞዴል ፈተና

**ለፈተናው የተሰጠ ሰዓት 1 ሰዓት**

## አጠቃላይ ትዕዛዝ

በዚህ የአካባቢ ሳይንስ ፈተና ዉስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛው መልስ የሆነዉን አራት አማራጭ ያዘዉን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠዉ ወረቀት ላይ መልስ ይሰጣል። በፈተናዉ ላይ የተሰጠዉን ትዕዛዝ በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናዉን መስራት አለብን ። ፈተናዉን ሠርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው። ፈተናዉን ሠርቶ ለመጨረስ የተሰጠዉ ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናዉን መስራት ማቆም አለብን። ፈተናዉ እንዴት እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ(ኟ) እስከ ሚነገር ድረስ ቦታችሁ በመቀመጥ መጠበቅ አለባችሁ። መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናዉን ሕግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናዉ አይያዝለትም እንዳይፈተን ይደረጋል። ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት መልስ በመስጫው ላይ መሞላት የሚገባዉን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሆነውን መልስ በመምረጥ መልስ መስጫው ወረቀት ላይ ፃፉ።**

*1. የአንድን ሀገር መገኛ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ከሚያዋስኑ ነገሮች ጋር በማነፃፀር የምንጠቀምበት ዘዴ የቱ ነዉ?*

*ሀ.ኬንትሮስ ለ. ፍፁማዊ መገኛ ሐ.አንፃራዊ መገኛ መ.ኬክሮስ*

*2. በካርታ ወይም በሉል ላይ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ወይም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ የሚሰመሩ የሀሳብ መስመሮች አጠቃላይ ብዛት ስንት ነው?*

*ሀ. 360 ለ.90 ሐ.185 መ.180*

*3. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሀገር ያልሆነዉ የቱ ነዉ ?*

*ሀ. ሱዳን ለ. ግብፅ ሐ.አንጎላ መ.ቦትስዋና*

*4. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ሀገር የሆነው የቱ ነዉ?*

*ሀ. ጂቡቲ ለ.ታንዛኒያ ሐ.ሩዋንዳ መ.ኬንያ*

*5. በሁለት የመሬት መሠንጠቅ መካከል ያለው ቦታ ወደ ላይ ሲነሳ የተፈጠረ ተራራ የቱ ነው ?*

*ሀ.ኪሊማንጃሮ ለ.ራስ ዳሸን ሐ. ሜሩ መ. ሩዋንዞሪ*

*6. የአንድን አካባቢ የገበያ ትስስር ለመፈለግ የሚያስችል መተግበሪያ ምን ይባላል?*

*ሀ. ጎግል ካርታ ለ.ጂፒኤስ ሐ.ጎግልኧርዝ መ.ስቴትስኮፕ*

*7. ሩቅ ያሉ ቦታዎችን ለማየት እና ለመመርመር የሚያገለግለው መሳሪያ የቱ ነዉ ?*

*ሀ.ጂፒኤስ ለ.ጎግል ካርታ ሐ.ጎግል ኧርዝ መ. ጎግል ማፕ*

*8. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ የቀይ የደም ህዋስ ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ?*

*ሀ.የጊዜ ርዝማኔያቸዉ ከ100 - 120 ቀን ነዉ. ሐ.በሽታ ይከላከላሉ*

*ለ. ቅርፅ አልባ ናቸው መ. ደም እንዲረጋ ያደርጋሉ*

*9. ከሚከተሉት ዉስጥ የልብ ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነዉ?*

*ሀ.ኦክስጅን እና ምግብ ለህብረ ህዋስ ማዳረስ ሐ.ካርቦን ክልቶ ኦክሳይድ እና ቆሻሻን ከሰዉነት ማስወገድ*

*ለ.ደም መርጨት መ.ደም ማጣራት*

10. ከሚከተሉት ውስጥ የፆታዊ ጥቃት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.አካላዊ ጉዳት ለ.ወሲባዊ ጥቃት ሐ. ስነ_ልቦናዊ ጥቃት መ. ለኢኮኖሚያዊ ጥቅም

11. ስለ ኑቢያ ጥንታዊ ስልጣኔ ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ ?

ሀ. የኑቢያ የመጀመሪያ መንግስት የኩሽ መንግስት ይባላል

ለ. የምስራቅ አፍሪካ ሁለተኛው ስልጣኔ ነው፡፡

ሐ.የኩሽ መንግስት ዋና ከተማ ናፓታ ይባላል ::

መ. በናይል ወንዝ ሸለቆ ዳርቻዎች እና በአሰዋን ፤በግብፅ ና በካርቱም መካከል ይገኛል፡፡

12. ከሚከተሉት ዉስጥ በምስራቅ አፍሪካ ዋና ቅርስ ውስጥ የሚመደበዉ የቱ ነዉ?

ሀ.የአብያተ መንግስታት ፍርስራሾች ና የመቃብር ሥፍራዎች ለ.መንፈሳዊ ቅርሶች

ሐ.ቁሳዊ ቅርሶች መ.የእምነት ሥርአቶች

13. በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ቀዳሚዉን ስፍራ የሚይዘዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ኢንዱስትሪ ለ.ግብርና ሐ.ቱሪዝም መ.እደ ጥበብ

14.ከሚከተሉት ዉስጥ በምስራቅ አፍሪካ የቅርስን አጠቃቀም ከሚቀንሱ ምክንያቶች ዉስጥ አይካተትም፡፡

ሀ.በቅርሶች አጠቃቀም ዙሪያ በቂ እቅድ አለመኖር

ሐ.ብቁ እና የሰለጠኑ አስጎብኝዎች አለመኖር

ለ.በቂ የሆነ እንክብካቤ ና ቁጥጥር አለመኖር

መ.የተፈጥሮ እና የሰው ሠራሽ አደጋዎች የማያሰጋቸው መሆናቸዉ

15. ከምስራቅ አፍሪካ አገሮች ዉስጥ የተሻለ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታ ያላት ሀገር ማን ናት?

ሀ.ታንዛኒያ ለ.ኢትዮጲያ ሐ.ሱዳን መ. ኬንያ

16.ከሚከተሉት ዉስጥ ቱሪዝም በምስራቅ አፍሪካ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረውን ፋይዳ የሚገልፀዉ የቱ ነው ?

ሀ.የሥራ አጥ ቁጥር ይጨምራል ሐ.ከዉጭ ሀገራት ጋር ያለውን ያዳክማል

ለ.የእደ-ጥበብ ሥራዎች ና ዉጤቶችን ያበረታታል መ.የሀብት ብክነት ይጨምራል፡፡

17.ከሚከተሉት ዉስጥ ከምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ዉስጥ የማይካተተዉ ሀገር የቱ ነው ?

ሀ.ኬንያ ለ.ሶማሊያ ሐ.ኤርትራ መ.ቦትስዋና

18. ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱ የድብልቅን ምንነት አይገልጽም ።

ሀ.ድብልቅ የሚፈጠረዉ በኬሚካላዊ መንገድ ነዉ

ለ.ምንዝሮቹ የራሳቸዉን ባህሪ ይ አይለዉጡም

ሐ.ድብልቁ ዉስጥ የሚገኙ ምንዝሮች በአይን ወይም በአጉሊ መነፅር መለየት ይቻላል

መ. ድብልቆች በሁለት ይከፈላሉ።

19. ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱ ዋህድ ዘር ድብልቅ ነዉ ?

ሀ.ወተት ለ. የጨዉ ሙሙት ሐ. ደም መ. የአሸዋ ና የዉሀ ድብልቅ

20. ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱ ታዳሽ ያልሆነ የጉልበት ምንጭ ምሣሌ አይደለም።

ሀ.የፀሀይ ብርሀን ለ.የድንጋይ ከሰል ሐ. የማገዶ እንጨት መ.የባትሪ ድንጋይ

21. ከሚከተሉት ዉስጥ የጉልበት ጥቅም የሆነው የቱ ነዉ ?

ሀ. ምግብ ለማብሰል ለ.ጊዜን ያባክናል ሐ.ድካም ይጨምራል መ. ወጪ ይጨምራል

22. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ ስለ ቀላል መኪና ጠቀሜታ የማይገልፀዉ የቱ ነዉ ?

ሀ. የሐይልን አቅጣጫ ይቀይራል ሐ.ጊዜ ያባክናል

ለ.ፍጥነትን ይጨምራል መ.ስራን በቀላሉ ለመስራት ይጠቅማል።

23. ከምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ዉስጥ ለግብርና ስራ በቂ የዝናብ መጠን ያላት ሀገር ማን ናት ?

ሀ.ሶማሊያ ለ. አፋር ሐ. ታንዛኒያ መ. ኤርትራ

24. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ በትክክል የተጣመረው የቱ ነዉ ?

ሀ. ከምድር ወገብ በስተደቡብ የሚገኙ የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የዝናብ ወቅት ከጥቅምት አስከ ሚያዚያ ወር ነዉ።

ለ.በምድር ወገብ አካባቢ ያሉ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ዝናብ የሚያገኙት ከታህሳስ እስከ የካቲት ነዉ።

ሐ.ከምድር ወገብ በስተ ደቡብ የሚገኙ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የዝናብ ወቅት በጥቅምት እና ሚያዚያ ወር ነዉ።

መ.በምስራቅ አፍሪካ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙ አካባቢዎች ዝናብ የሚያገኙት ከሰኔ እስከ መስከረም ነዉ።

25. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የምስራቅ አፍሪካን ዉጤታማ የተፈጥሮ ወጤታማ አጠቃቀም ዘዴ የማይመደበዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በቤት ዉስጥ ዉሀን በአግባቡ መጠቀም

ለ. በወንዞች አካባቢ እፅዋትን መትከል

ሐ. ባዮ ጋዝ ን መጠቀም

መ. ስለተፈጥሮ ሀብት ኢያያዝ የወጡ ሕግ ና ደንቦችን አለመተግበር

26. ከሚከተሉት ዉስጥ ሰለምስራቅ አፍሪካ ዉጤታማ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምንነት የሚገልፀዉ ሀሳብ የቱ ነዉ?

ሀ. በአንድ አካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባብ በመጠቀም ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ማድረግ

ለ. የተፈጥሮ ሚዛን እንዲዛባ ያደርጋል

ሐ. የተፈጥሮ ሀብቶች አህጉራዊና ቀጠናዊ ምጣኔ ሀብትን ለማሳደግ አነስተኛ ሚና አላቸዉ

መ. የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ አለመጠቀም

27. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ አንዱ የአፈር መሸርሸር መንስኤዎች ዉስጥ አይካተትም ::

ሀ. እርከን መስራት ለ.የአፈር አይነት ሐ. የመሬት አቀማመጥ መ.የእፅዋት ሽፋን መመናመን

28.. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ የአፈር አጠባበቅ ዘዴ ዉስጥ አይመደብም::

ሀ.ድነና ለ.ደን መጨፍጨፍ ሐ.ጣምራ የደን እርሻ መ.አዝዕርትን ማፈራረቅ

29. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ የምስራቅ አፍሪካ የዉሀ ሀብት አጠቃቀም ችግር የሆነዉ የቱ ነዉ ?

ሀ.ድርቅ እና የአየር ንብረት መዛባት

ለ.ዉሀማ አካላት ላይ የሚጨመሩ የፕላስቲክ እና መርዛማ ኬሚካሎች ማነስ

ሐ.በጋራ የዉሀ ተፋሰስ ሀገራት ፍትሐዊ የዉሀ ሀብት አጠቃቀም መኖር

መ.ውሃን ሳያባክኑና ሳይበክሉ መጠቀም

30. በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ የማዕድን ዓይነቶች ዉስጥ በስፋት የሚገኝ የማዕድን የቱ ነዉ?

ሀ.ጨዉ ለ.ሸክላ አፈር ሐ.ኒኬል መ. ወርቅ

31. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ በምስራቅ አፍሪካ ለማዕድን ሀብት መመናመንን የሚያባብስ ሁኔታ አይካተትም ::

ሀ.ማዕድን በባህላዊ መንገድ ማዉጣት ሐ. ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባብ አለመጠቀም

ለ.ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀም መ. በእቅድ ና በመመሪያ አለመመራት

32. ከምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች መካከል በህዝብ ብዛት ከአንድ እስከ ሦሥት የያዙ ሀገራት እነማን ናቸዉ ?

ሀ.ኤርትራ ፣ጂቡቲ ና ሞሪሽየስ ሐ.ኢትዮጲያ ፣ኬንያ ና ታንዛንያ

ለ.ኢትዮጲያ ፣ታንዛኒያ ና ኬንያ መ.ኢትዮጲያ ፣ታንዛንያ ና ዩጋንዳ

33. ለአየር ወደ አየር ከረጢት መግቢያ እና መዉጫ በመሆን የሚያገለግል የመተንፈሻ አካል ክፍል የቱ ነዉ ?

ሀ.ሰርን ለ ድህረ አፍ ሐ.ደቂቅ ትንቧ መ.ዐብይ ትንቧ

34. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ በምስራቅ አፍሪካ ከሚከናወኑ ዐብይ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የማይመደበዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ሆርቲካልቸር ለ. ግብርና ሐ.የማዕድን ቁፋሮ መ. ትላልቅ ኢዱስትሩዎች መኖር

35. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ ኤች አይቪ /ኤድስ በምስራቅ አፍሪካ ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ ውስጥ አይካተትም

ሀ. የአምራቾች ቁጥር ይጨምራል ሐ. የጤና ቀዉስ ያስከትላል

ለ. የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከትላል መ. በማህበራዊ ኑሮ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል

36. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከአደንዛዥ እፅ ወስጥ አይመደብም

ሀ.አልኮል ለ.ሲጋራ ሐ.ጫት መ . ሻይ

37. ከሚከተሉት አማራጮች ወስጥ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት እንዳይከሰት መድረግ ያለብን ቅድመ ጥንቃቄ የሆነዉ የቱ ነዉዉ?

ሀ.ጠለፋ ሐ. ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት

ለ. የሴት ልጅ ግርዛት መ. ያለዕድሜ ጋብቻ

38. ከሚከተሉት  አማራጮች ዉስጥ  በምስራቅ አፍሪካ ድርቅን  ለመቋቋም  የሚያስችል ዘዴ የሆነዉ  የቱ ነዉ?

ሀ.ችግኝ አለመትከል      ሐ.የምስራቅ አፍሪካ  ቀጠናዊ ፣ሰላም ና ልማታዊ ትስስርን  ማጠናከር

ለ. መስኖ  የመጠቀም ልምድ አለማዳበር          መ.ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴ መጠቀም

39. አየር በማሞቅ  ቆሻሻን ና ጀርምን በማጣራት  የሚታወቀዉ የመተንፈሻ አካል ክፍል  ምን ይባላል?

ሀ.አፍንጫ        ለ. ሰርን          ሐ. ድህረ-አፍ            መ.ተገንጣይ ትንቧ

40. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ  የተፈጥሮ ሀብት   የተሻለ ዘዴ  የሆነው የቱ  ነው?

ሀ.ሀገር በቀል እፅዋትን መትከል ና መንከባከብ     ሐ.የተፈጥሮ ሀብትን አለመቆጠብ

ለ. ምግብን ለማብሰል እፅዋቶችን መጠቀም       መ.አማራጭ የጉልበት ምንጮችን አለመጠቀም